# የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ ቁጥር 908/2014

Cement Marketing and Distribution Directive No. 908/2014


የንግድ እና ቀጠናዊ ትስስር ሚኒስቴር

Ministry of Trade and Regional Integration


ሰኔ 17፥ 2014

**መግቢያ**

በሀገራችን የግንባታ ዘርፍ ማደግን ተከትሎ የሲሚንቶ ምርት በተለያዩ ውጫዊና ውስጣዊ ምክንያቶች በአቅርቦትና ፍላጎት መካከል ያለ ልዩነት እየሰፋ የዋጋ ንረቱ እንዲባባስ ምክንያት መሆኑና ቅድሚያ የሚሰጣቸውና ተጠናቀው ለመንግስትና ለህዝብ አገልግሎት መስጠት የሚገባቸው የግንባታ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልጋቸውን የሲሚንቶ ግብዓት ማግኘት አልቻሉም፡፡

ስለሆነም የሲሚንቶ ምርታማነት በመጨመር ግብይቱ በነጻ የገበያ ስርዓት እስኪመራ ድረስ ስለ ተመረተው ምርት ስርጭት ቅደም ተከተል ማስቀመጥና ለመንግስት ግንባታ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ በመሆኑ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የኢፌዲሪ አስፈጻሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 1263/2014 ዓ.ም አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ እና ለ) ለማስፈጸም ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የሲሚንቶ ግብይትና ስርጭት መመሪያ ቁጥር 908/2014" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. የቃላት ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"ሚኒስቴር"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ማለት ነው፤
2) **"ክልል"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ሲባል የአዲስ አበባ እና የድሬደዋ ከተማ አስተዳደርንም ይጨምራል፤
3) **"የሚመለከተው የመንግስት ተቋም"** የግንባታና ኮንስትራክሽን ስራዎችን የሚመራና የሚከታተል የፌደራልና የክልል የመንግስት ተቋም ነው፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በሀገር ውስጥ የሲሚንቶ ምርት የሚያመርቱ አምራቾች፣ የመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች፣ የሲሚንቶ ግብይት እንዲያካሂዱ በክልል የተፈቀደላቸው የልማት ድርጅቶች፣ የተለያዩ ማህበራት እና እንደአስፈላጊነቱ የግል ገንቢዎች የወሰዱትን ምርት ከታለመው ውጭ ለገበያ የሚያውሉት ከሆነ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

# ክፍል ሁለት

# ግዴታዎች

## 4. የሲሚንቶ አምራቾች ግዴታ

1) ከክልልና ከከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮዎችና ከሲሚንቶ አምራችች ማህበር ጋር በመነጋገር ከተሞችን መለየትና የመሸጫ ማእከላትን ማዘጋጀት አለባቸው፣
2) በፌደራል ደረጃ ለሚገነቡ ሜጋ የመንግስት ፕሮጀክቶች ቅድሚያ በመስጠት መጠኑ በሚመለከተው የመንግስት ተቋም እየተረጋገጠ ሲሚንቶ በቀጥታ ከፋብሪካ እንዲያገኙ ማድረግ አለባቸው፣
3) በየክልሉ በመንግስት ለሚገነቡ ግንባታ ፕሮጀክቶች በከተሞች በሚከፈቱ የሲሚንቶ መሸጫ ማእከላት ትክክለኛ መጠኑ በሚመለከተው የመንግስት ተቋም እየተረጋገጠ በቀጥታ ቅድሚያ በመስጠት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣
4) እያንዳንዱ የሲሚንቶ ፋብሪካ የሚያቀርበውን የሲሚንቶ ምርት በመሸጫ ማእከል እና በሌሎች ከተሞች የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ ይወስናል፣ ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ያሳውቃል፣
5) ለሲሚንቶ ምርት ሽያጭ በቅድሚያ ያስከፈላችሁትን ክፍያ ከተወሰደ አንድ ሳምንት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የሲሚንቶ ምርት ማስረከብ ይኖርባቸዋል፣
6) በማህበር ለተደራጁ የአካባቢ ወጣቶች ከሚመረተው የሲሚንቶ ምርት በልዩ ሁኔታ ከ20 እስከ 30 በሙቶ ሽያጭ ይፈጽማል፣
7) የተመረተው ምርት መጠንና የተሸጠላቸውን አካላት መረጃ በየወሩ በማደራጀት ለሚኒስቴር መስሪያቤት መላክ፣

## 5. የሲሚንቶ አምራቾች ማህበር ኃላፊነት

1) ከክልሎች እና ፋብሪካዎች ጋር በመነጋገር የክልልና ከተማ አስተዳደር የሽያጭ ማዕከላትን ይወስናል፣
2) በፌደራልና በክልል መንግስት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ብዛትና የሲሚንቶ ፍላጎትን መሰረት ያደረገ በሲሚንቶ ፋብሪካ እና በየመሸጫ ማእከላት የሚቀርበውን የሲሚንቶ መጠን ከፋብሪካዎች ጋር በመሆን ይወስናል፣
3) የፋብሪካ በርና የመሸጫ ማዕከላት እንዲሁም የሌሎች ከተሞች የሲሚንቶ መሸጫ ዋጋ ግንባታ ተመጣጣኝ መሆኑን ያረጋግጣል፣
4) ወርሃዊ የሲሚንቶ ምርት ስርጭት መረጃን ከፋብሪካዎች በመቀበልና በማጠናቀር ለሚኒስቴር መስሪያቤት ሪፖርት ያቀርባል፣

## 6. በፌደራልና በክልል መንግስታት የሚገነቡ የግንባታ ፕሮጀክቶች ኃላፊነት

1) ለግንባታ የሚስፈልገውን የምርት መጠን በሚመለከተው የመንግስት ተቋም ትክክለኛነቱ ተረጋግጦ ለሲሚንቶ ፋብሪካዎች እና ለሲሚንቶ አምራቾች ማህበር ማቅረብ፣
2) በፌደራል መንግስት ባለቤትነት ለሚመሩ የግንባታ ፕሮጀክቶች ከተመደቡበት አምራች ፋብሪካዎች በቀጥታ ይገዛሉ፣
3) በክልል መንግስት ባለቤትነት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች አምራች ፋብሪካዎች ምርቱን በሚያቀርቡበት የክልል/የከተማ አስተዳደር የሲሚንቶ መሸጫ ማእከል በቀጥታ ይገዛሉ፣
4) ለግንባታ የሚወስዱትን የሲሚንቶ ምርት ለታለመለት አላማ ብቻ ማዋል ይኖርባቸዋል፡፡

## ክፍል ሶስት

## ግዴታዎች

### የሚኒስቴሩና በክልል ንግድን ለማስተዳደር በህግ ስልጣን የተሰጠው አካል ተግባርና ኃላፊነት

## 7. የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር ተግባርና ኃላፊነት

1) የሲሚንቶ ምርት ስለሚሰራጭበት ሁኔታ በየጊዜው በመፈተሽ እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ የአሰራር ስርአት ይዘረጋል፣
2) በዚህ መመሪያ ላይ የተቀመጡትን አሰራሮች በተገቢው ስለመፈጸሙ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣
3) በአምራች ፋብሪካዎችና በከተሞች በሚከፈቱ የመሸጫ ማእከላት ቅድሚያ ለመንግስት ግንባታ ፕሮጀክቶች መሸጡን ያረጋግጣል፣
4) የሲሚንቶ ምርት መጠን፣ የስርጭትና የመሸጫ ዋጋ መረጃዎችን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣

## 8. በክልልና በከተማ አስተዳደር ንግድን የሚያስተዳድሩ ቢሮዎች ኃላፊነት

1) በክልልና በከተማ አስተዳደር የሲሚንቶ መሸጫ ማእከላት የሚዘጋጅላቸው ከተሞች/ቦታዎች መለየት እና ከፋብሪካዎችና ከሲሚንቶ አምራቾች ማህበር ጋር በመሆን ማመቻቸት፣
2) በተመረጡ የመሸጫ ማእከላት እና በሌሎች ሁሉም ከተሞች የሲሚንቶ ፋብሪካው በተመነው ዋጋ መሰረት ስለመሸጡ መከታተል፤መቆጣጠር፣
3) የሲሚንቶ ስርጭት ለመንግስት የግንባታ ፕሮጀክቶች ቅድሚያ እየተሰጠ መሆኑና ለታለመለት ዓላማ መዋሉን ያረጋግጣል፣
4) በየክልል ከተሞች በሚከፈቱ የሲሚንቶ መሸጫ ማእከላት በመንግስት ከሚገነቡ የግንባታ ፕሮጀክቶች የሚተርፈውን መጠን ለሌሎች ገንቢዎች በቀጥታ የሚሸጥበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ይቆጣጠራል፣

5) የመሸጫ ማእከል በሌለባቸው አካባቢዎች ከመንግስት የግንባታ ፕሮጀክት የሚተርፈውን የሲሚንቶ ምርት ለሌሎች ገንቢዎች እንደቅደም ተከተላቸው የሚሰራጭበትን የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤ያሳውቃል፣

## ክፍል አራት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. አስተዳደራዊና ህጋዊ እርምጃ

ይህንን መመሪያ በሚተላለፉ ላይ አግባብነት ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 10.የመተባበር ግዴታ

የዚህ መመሪያ አፈጻጸም ሁሉም አካል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 11.የተሻሩ መመሪያዎች እና አሰራሮች

"የሲሚንቶ አቅርቦትና ግብይት መመሪያ ቁጥር 23/2012 ዓ.ም" የሲሚንቶ ግብይትን የሚመለከቱት ሁሉም ድንጋጌዎች በዚህ መመሪያ ቁጥር 908/2014 ተሽረዋል፡፡

### 12.መመሪያውን ስለማሻሻል

ሚኒስቴሩ ይህንን መመሪያ እንደአስፈላጊነቱ ሊያሻሽል ወይም ሊሰርዝ ይችላል፡፡

### 13.መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከሰኔ 17/2014 ዓ.ም ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

**ገብረመስቀል ጫላ ሞጣሎ**

**ሚኒስትር**

**የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር**